መዝሙረ ዳዊት 91

የዳዊት የምስጋና መዝሙር።

1 በልዑል መጠጊያ የሚኖር ሁሉን በሚችል አምላክ ጥላ ውስጥ ያድራል።
2 እግዚአብሔርን፦ አንተ መታመኛዬ ነህ እለዋለሁ አምላኬና መሸሸጊያዬ ነው፥ በእርሱም እታመናለሁ።
3 እርሱ ከአዳኝ ወጥመድ ከሚያስደነግጥም ነገር ያድንሃልና።
4 በላባዎቹ ይጋርድሃል፥ በክንፎቹም በታች ትተማመናለህ እውነት እንደ ጋሻ ይከብብሃል።
5 ከሌሊት ግርማ፥ በቀን ከሚበርር ፍላጻ፥
6 በጨለማ ከሚሄድ ክፉ ነገር፥ ከአደጋና ከቀትር ጋኔን አትፈራም።
7 በአጠገብህ ሺህ በቀኝህም አሥር ሺህ ይወድቃሉ ወደ አንተ ግን አይቀርብም።
8 በዓይኖችህ ብቻ ትመለከታለህ፥ የኃጥኣንንም ብድራት ታያለህ።
9 አቤቱ፥ አንተ ተስፋዬ ነህና ልዑልን መጠጊያህ አደረግህ።
10 ክፉ ነገር ወደ አንተ አይቀርብም፥ መቅሠፍትም ወደ ቤትህ አይገባም።
11 በመንገድህ ሁሉ ይጠብቁህ ዘንድ መላእክቱን ስለ አንተ ያዝዛቸዋልና
12 እግርህም በድንጋይ እንዳትሰናከል በእጆቻቸው ያነሡሃል።
13 በተኵላና በእባብ ላይ ትጫማለህ አንበሳውንና ዘንዶውን ትረግጣለህ።
14 በእኔ ተማምኖአልና አስጥለዋለሁ ስሜንም አውቆአልና እጋርደዋለሁ።
15 ይጠራኛል እመልስለትማለሁ፥ በመከራውም ጊዜ ከእርሱ ጋራ እሆናለሁ አድነዋለሁ አከብረውማለሁ።
16 ረጅምን ዕድሜ አጠግበዋለሁ፥ ማዳኔንም አሳየዋለሁ።



የልዑል እግዚአብሔር ቸርነቱና ምሕረቱና ከሁላችን ጋር ይሁን።

የቅዱስ ገብርኤል ረድኤቱና በረከቱ አይለየን....... አሜን።